ገዳይ ቢዘገይ ሟች ይገሰግሳል

ሟች ወያኔ ገዳይ ሱማሌ ነው። ወያኔ ወደ መጥፊያው እየገሰገሰ ነው። ይህ የወያኔ መጥፋት የሁላችንም ጸሎትና ትግል ነበር አሁንም ነው። ችግሩ ግን ወያኔ ብቻ ሳይሆን የሚጠፋው ሀገራችን ኢትዮጵያና ያ ኩሩ ህዝባችን እንዳይሆን ነው ከፍተኛ ስጋቴ። ወያኔ ነብስ አውቆ ጥይት መተኮስ ከጀመረ ማግስት ኢትዮጵያን ከማጥፋትና የሚኖርበትን ቤት ከማፍረስ የተኛበት ጊዜ የለም። በሽፍትነትም ሆነ በሃገር መሪነት፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያችን ጥንታዊት ሃገርና ያንን ኩሩ ህዝብ አዋርዶታል፤ ዘርፎታል፤ገድሎታል። አሁን ደግሞ በስመ ሽብርተኝነት ስም የቀረ ህዝብና ሃገር ለማስጨረስ በመራወጥ ላይ ይገኛል።

ይህ ወያኔ በሱማሌ የውስጥ ጉዳይ ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት በውዲቱ ሀገራችንና በዚህ መከረኛ ህዝባችንን ላይ የሚያመጣው ጦስና መዘዝ በህሊና ሊታሰብ ከሚችለው በላይ መሆኑን ማወቅ ነብይነት አይጠይቅም። በተለያዩ የዜና አውታሮች የምናየው የምንሰማው የዕለት ተዕለት ክስተት ብቻ ሳይሆን ወያኔን ጠንቅቆ ለሚያውቅ ጤነኛ ኢትዮጵያዊ የሁኔታውን ውስብስብነት ለመረዳት አያስቸግረውም። ወያኔ እየጠፋ ሀገራችንንም ሊያጠፋ ነው። ኢትዮጵያን እወዳለሁ የሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጋራ ሊመክርብት፤ ሊነሳሳና አፋጣኝ እርምጃ ከወዲሁ ሊወሰድበት የሚገባ ለነገ የማይባል ወቅታዊና ሃገራዊ ግዳጅ ነው እላለሁ።

በልቶ የማይጠገበው ወያኔ በምስራቅ የሀገራችን ክፍል ያለውን የመገንጠል አደጋ በማስታከክ የስልጣን እድሜውን ለማስረዘምና ከታላላቅ ሀገሮች የተሰጠውን "የቤት ሥራ" ለመፈጸም የሚያደርገው ሽር ጉድ ከወዲሁ ማክሸፍ መቻል ይገባናል። የኢትዮጵያ መኖርና መበልጸግ የማይዋጥላቸው መሠረታዊ ጠላቶቻችን በቅርብ ጊዜያት በመጀመሪያ ጀበሃን፤የዚያድ ባሬን መንግሥት፤ ሻዕቢያ ከዚያም ራሱን ወያኔን አሁን ደግሞ በሱማሌ በኩል ሽብርተኞችን እያደራጁና እያስታጠቁ ሰላም የነሱን ዛሬ አይደልም። የቆየ የተለመደ ተግባራቸው ነው። ሆኖም ግን በየጊዜው የተነሱ የሃገራችን መሪዎች ሁኔታዎችን እያስተዋሉ፤ የአለም አቀፍ አንድምታዎችን እያንሰላሰሉ መከላከል በሚያስፈልግበት ጊዜ እየተከላከሉ፤ ዲፕሎማሲው አስፈላጊነቱ በሚያይለበት ወቅት በዲፕሎማሲው ጎዳና እየተጓዙ ሃገሪቱንና ሕዝቡን ለዛሬው ጊዜ አደርሰውልናል። ኃይል መጠቀም ጥፍቷቸው ወይንም አቅቷቸው አልነበርም። ሆኖም ግን ያንን አጋጣሚ ተጠቅመው ኢትዮጵያን በቀጥታ ማጥፋት ሁሌም በቋፍ ላይ ለሚገኙት ጠላቶቻችን በር ላለመክፈትና ሃገሪቱን ለበለጠ አደጋ ላለማጋለጥ እንደነበር ሁሉም የሚገነዘበው ይመስለኛል።

እኩዩ ወያኔ አክራሪ እስላሞችና በኡጋዴን በኩል ያሉ ተገንጣዮች አደጋ ሊያደርሱብን ነው በሚል ፈሊጥ ወደ ሱማሌ የሚያደርገው የክተት ጥሪ መደርግ ቢያስፈልግ ኑሮ

ከዛሬ 30 ዓመት በፊት በሱማሌና በሱዳን ላይ ተፈጻሚ መሆን ይገባው ነበር። ግን ከላይ በጠቀስኩት ምክንያት በቀጥታ ድንበር አልፈው እስካልመጡ ድረስ የተወሰድ እርምጃ አልነበርም።

አሁን ወያኔ የሚያናፋው ጩኸትና ተደፈርኩ ባይነት በሱማሌና በሱዳን መንግሥታት ከተፈጸመው በልጠ ሳይሆን

ሀ/ ተጭበርበሮ ከሕዝብ የተቀማ ሥልጣን አጭበርብሮ ይዞ የስልጣን እድሜውን ለማስረዘምና
ለ/ ከጌቶቹ የተሰጠውን "የቤት ሥራ" ፈጽሞ ደጎስ ያለ የገንዘብ ዳረጎት ለመቸርፈስ ነው የሚለውን የብዙዎችን የፖለቲካ ተንታኞች ሃሳብ እስማማበታለሁ።

ውጤቱ ግን ሊታይ እንደሚችለው ከሥልጣኑም ከገንዘቡም ሳይሆን እንደሚቀር ጥርጥር የለውም። ለምን ቢሉ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተጣልቷልና! ዘመቻው ጸረ ሱማሌ ሳይሆን ጸረ ኢትዮጵያ ዘመቻ በመሆኑ ነው።

ይህንን ሁኔታ ለማክሸፍ በጋራ ጸረ ወያኔ ኃይሎችን የሚያስተባበር አንድ ግብረ ኃይል በአለም አቀፍና በብሔራዊ ደረጃ ተቋቁሞ የወያኔን ኢትዮጵያን የመግድል የመጨረሻ ሙከራ ማክሸፍ አለበት እላለሁ። ወያኔ ወደ መጥፊያው እየገሰገሰ ነው። ሀገራችንን ግን ይዟት እንዳይሞት ዛሬ ነገ ሳንል በጋራ እንነሳ። ይህንንም ታሪካዊ ተልዕኮ አሁን የሃገሪቱን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በመምራት ላይ ያሉ ነባርና በሳል የፖለቲካ ድርጅቶች ውጥኑን (initiative) መጀመር ይጠበቅባቸዋል።

አጥፊዎቹ ቢዘገዩም ወያኔ ወደ ሞቱ እይሮጠ ነው። ሻዕቢያም ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ የቀረ ሕዝብና ሃገር ለማጥፋት እያደባ ነው።

ኢትዮጵያችን እንዳትጠፋ ሕዝቧም እንድጨው ዘር እንዳይበተን ግን እንጠንቀቅ፤ እንትጋ!!

የኢትዮጵያ አምላክ ሀገራችንን በቸርነቱ ይጠብቅልን።

ታማኝሰው በለጠ
ሕዳር 17 ቀን 1998 ዓ.ም
tamagnsew@post.com